# የዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ሲፒርየር ፍርድ ቤት

## ትእዛዝ

## (በ11/05/20 የተሻሻለው)

በማርች 18፣ 2020 በተላለፈውና በመይ 29፣ 2020 ዳግም በተረጋገጠው ትእዛዝ መሰረት፣ ጆይንት ኮሚቲ ኦን ጁዲሽያል አድሚኒስትሬሽን (የፍትህ አስተዳደር የጋራ ኮሚቴ) አሁን ባለው የዳኝነት አስቸኳይ ጊዜና ለፍትህ አስተዳደርም የተሻለ ስለሆነ፣ በዲ.ሲ. ኮድ እና በሱፒርየር ፍርድ ቤት ደንቦች ያሉ ሁሉም የህግ እና ደንብ-ተኮር የጊዜ ገደቦች ታግደው፣ ለጊዜው ከተፈጻሚነት ቆመው (ቶል ተደርገው) እና ተራዝመው የሚቆዩበት የጊዜ ገደብ ለማራዘም የሚያስችሉ ትእዛዞች ለማስተላለፍ ለዋናው ዳኛ (ቺፍ ጃጅ) ስልጣን ሰጥቷል።

በማርች 18፣ 2020፣ በማርች 19፣ 2020፣ በመይ 14፣ 2020፣ በጁን 19፣ 2020፣ እና በኦገስት 13፣ 2020 በተላለፉት ትእዛዞች ዋናው ዳኛ (ቺፍ ጃጅ) እንደሚከተለው ብሎ ነበር (በግልጽ ካልተጠቀሰ በስተቀር)፡ ሁሉም ከጁን 19፣ 2020 በፊት እንዲፈጸሙ በህጎች፣ በፍርድ ቤት ደንቦች፣ እና ፍርድ ቤት ባስተላለፋቸው እና በሌሎች ትእዛዞች የሰፈሩ የጊዜ ገደቦች፣ የአሁኑ የዳኝነት አስቸኳይ ጊዜ በስራ ላይ እስካለ ድረስ ይታገዳ፣ ከተፈጻሚነት ለጊዜው ይቆሙ (ቶል ይደረጉ)፣ እንዲሁም ደግሞ ይራዘሙ ዘንድ ታዝዟል። በትእዛዙ እንደተመለከተው፣ የጊዜ ገደቦቹ፣ ሁኔታዎች ሲቀየሩ ለተጨማሪ ጊዜ ሊታገዱ፣ ከተፈጻሚነት ለጊዜው ሊቆሙ (ቶል ሊደረጉ)፣ እንዲሁም ደግሞ ሊራዘሙ ይችላሉ። እገዳው፣ ከተፈጻሚነት ለጊዜው መቆሙ (ቶል መደረጉ)፣ እና መራዘሙ በዚህ ትእዛዝ በሰፈረው መሰረት ቢያንስ እስከ ጃንዋሪ 15፣ 2021 ድረስ ይቀጥላል። ፍርድ ቤቱ ሁሉንም እገዳዎች፣ ከተፈጻሚነት ለጊዜው መቆሞች (ቶል መደረግ) እና የመራዘሚያ የጊዜ ገደቦች ከማብቃታቸው ቢያንስ ከ60 ቀናት በፊት ማስታወቂያ ያቀርባል።

ፍርድ ቤቱ እስከ ጃንዋሪ 15፣ 2021 ድረስ የሚሰማቸው የጉዳዮች አይነቶችና ቁጥር በማስፋት ይገኛል።

የፍርድ ቤት ሰራተኞች፣ ጠበቆች፣ ባለ ጉዳይ አካላት፣ እና የህብረተሰብ አባላት ደህንነትና ጤና ይጠበቅ ዘንድ፣ ከተወሰኑት የወንጀለኛ ክፍል እና የቤት ውስጥ ብጥብጥ ችሎቶች በስተቀር፣ ሁሉም የጉዳይ አይነቶች በርቀት (ሪሞትሊ) ይሰማሉ፣ በርቀት የማይሰሙትም በከፊል በርቀት የሚካሄዱ ይሆናሉ።

የጉዳዩ አይነት ከታች እስካልተዘረዘረ ድረስ፣ ሁሉም እስከ ጃንዋሪ 15፣ 2021 ድረስ ተቀጥረው የነበሩ ቅድሚያ-የማይሰጣቸው (ናን-ፕራዮሪቲ) ጉዳዮች ተለዋጭ ቀጠሮ ይሰጣቸዋል፣ አዲስ ቀን ቀጠሮ ይያዝላቸዋል፣ አስቸኳይ የሆኑ ጉዳዮች ተይዞላቸው ባለ የፍርድ ቤት ቀጠሮ ይቀጥላሉ፣ ከታች እንደተቀመጠውምም ይሰማሉ። ጉዳዮቹን የሚሰሙ

ዳኞች እንደየ አስፈላጊነቱ ስለሚሰሟቸው ጉዳዮች በተመለከተ ተጨማሪ ትእዛዞች ያስተላልፋሉ።

የኮቪድ-19 ምልክቶች ያለባቸው ማንኛቸውም ጠበቃም ይሁን ሰዎች ወደ ፍርድ ቤት በአካል መግባት የለባቸውም። https://www.cdc.gov/coronavirus/2019-ncov/about/symptoms.html ይመልከቱ።

ማንኛውም ከነዚህ ለውጦች እፎይታ (ረሊፍ) መጠየቅ የሚፈልግ አካል በተገቢው ፍርድ ቤት ማመልከቻ ፋይል በማድረግ እፎይታ ይሰጠው ዘንድ መጠየቅ ይችላል።

ፋይል ለሚደረጉ ማመልከቻዎች (ፐሊዲንግስ)፣ አቤቱታዎችና አዳዲስ ጉዳዮች ለመቀበል፣ ሁሉም ክፍሎችና (ዲቪዥንስ) የቤተሰብ ፍርድ ቤት በርቀት (ሪሞትሊ) ክፍት ይሆናሉ። በኤሌክትሮኒካዊ መንገድ ፋይል ማድረጉ ይቀጥላል። ዝርዝር መረጃ ለማግኘት የጸሀፊ ቢሮዎች (ክለርክ'ስ ኦፊስስ) የርቀት ክወናዎች (ሪሞት ኦፐሬሽንስ) ማስታወቂያዎችን ይመልከቱ። http://www.dccourts.gov/coronavirus

ፍርድ ቤቱ በዚህ ወቅት በተወሰኑ ሁኔታዎች ክፍያዎች በኤሌክትሮኒካዊ መንገድ በመቀበል ይገኛል። ለበለጠ ዝርዝር መረጃ https://www.dccourts.gov/services/online-payment ይመልከቱ።

በሕግ እስከ ተፈቀደ ድረስ፣ በርቀት የሚደረጉ ችሎቶች ለማህበረሰብ አባላት ቀጥተኛ ተደራሽነት ይኖራቸዋል። በርቀት በሚደረጉ የፍርድ ቤት ችሎቶች በቀጥታ እንዴት መስማት/መከታተል እንደሚቻል ሂደቱን የሚያሳይ መረጃ በፍርድ ቤቱ ድረገጽ ተለጥፏል። https://www.dccourts.gov/services/remote-hearing-information

ፍርድ ቤቱ እንደየ ሁኔታዎቹ ተጨማሪ ማስተካካያዎች ያደርጋል። አብዛኛዎቹ የፍርድ ቤት ክፍሎች በርቀት ለሚከናወኑ ስራዎች (ሪሞት ኦፐሬሽንስ) ጥቅም ሊውሉ ይችላሉ፣ ፍርድ ቤቱ ለተቀሩት የፍርድ ቤት ክፍሎች በተቻለ መጠን በቅርቡ ተገቢውን መሳሪያ ይገጥማል። ተጨማሪ የፍርድ ቤት ክፍሎች ለችሎት ክፍት እየሆኑ ሲመጡ የያንዳንዱ ክፍል ጉዳዮች የሚዳኙ ዳኞች ቀነ ቀጠሮ የሚያዝላቸውና የሚሰሟቸው ጉዳዮች ሊያሳውቁ ይችላሉ።

ፍርድ ቤቱ በሚከተሉት ሁኔታዎች በዋናነት በርቀት (ሞስትሊ ሪሞትሊ) ይሰራል፡

## <u>የፍትሐብሔር ክፍል (ሲቪል ዲቪዥን)</u>

በፍርድ ቤቱ ካልታዘዘ በስተቀር፣ በአስቸኳይ ጊዜ እንዲፈጸሙ በህጎች (ክስ የሚቀርብባቸው የጊዜ ገደቦችም (ስታቹ ኦፍ ሊሚቴሽን) ጭምር)፣ በፍርድ ቤት ደንቦች፣ እና ፍርድ ቤት ባስተላለፋቸው እና በሌሎች ትእዛዞች የሰፈሩ የጊዜ ገደቦች የአስቸኳይ ጊዜ በስራ ላይ እስካለ ድረስ ይታገዳሉ፣ ከተፈጻሚነት ለጊዜው ይቆማሉ (ቶል ይደረጋሉ)፣ እንዲሁም ደግሞ ይራዘማሉ። እንዲህ የማይሆንባቸው የሚከተሉት ልዩ ሁኔታዎች አሉ፡ (1) የፍርድ ቤት መጥሪያ ማድረሻ ገደብ (ሰርቪስ ኦፍ ፕሮሰስ) በስተቀር፣ በሂደት ባሉ ጉዳዮች በጠበቃ የተወከሉ አካላት የሚመለከቱ የጊዜ ገደቦች፣ (2) በጠበቃ ላልተወከሉ አካላት ጭምር የሚመለከት ለሁሉም አካላት የሚመለከቱ ከግኝት (ዲስካቨሪ) ጋር የተያያዙ የጊዜ ገደቦች፣ (3) በኖቨምበር 10፣ 2020 ወይም ከዚህ ቀን በኋላ ፋይል ለተደረጉ አቤቱታዎች፣ በጠበቃ ላልተወከሉ አካላት ጨምሮ ለሁሉም አካላት የሚመለከቱ ከአቤቱታዎች ጋር ተያያዥነት ያላቸው የጊዜ ገደቦች፣ እና (4) ከማርች 18፣ 2020 በኋላ በተላለፉ ትእዛዞች ያሉ የጊዜ ገደቦች። የዚህ ትእዛዝ ሌላ አንቀጽ ምን ይበል ምን፣ በሱፒርየር ፍርድ ቤት የአከራይና ተከራይ ቅርንጫፍ የስነ ስርአት ደንቦች (ሩልስ ኦፍ ፕሮሲጀር) ደንቦች (ሩልስ) 16(a)(4) እና 16(c) መሰረት ከመኖሪያ ቤት ማስወጫያ ትእዛዝ (ሪትስ ኦፍ ረስቲቱሽን) ትክክለኛነት እና መስጠት የተመለከቱ በአስቸኳይ ጊዜ አገልግሎታቸው ያበቃ የነበረ የጊዜ ገደቦች የአስቸኳይ ጊዜ ተፈጻሚ እስከሚሆንበት ጊዜ ድረስ ይታገዳሉ፣ ለጊዜው ከተፈጻሚነት ይቆማሉ (ቶል ይደረጋሉ)፣ እና ይራዘማሉ።

የፍትሐብሔር ክፍል በሚከተለው መልኩ ይሰራል፡

- ዳኞችና የክፍሉ ሰራተኞች (ዲቪዥን ስታፍ) በርቀት መስራት ይቀጥላሉ። ዳኞች በምናባዊ (ቨርቹዋል) የፍርድ ቤት ክፍሎች ችሎቶች በሳምንት ለአምስት ቀናት ያህል በርቀት ያካሂዳሉ። በአካል እንዲቀርቡ በዳኛው ካልታዘዙ በስተቀር ማናቸውም አካላት ወይም ጠበቆች በአካል መቅረብ የለባቸውም።

- ማናቸውም የአስቸኳይ ማመልከቻ (ኢመርጀንሲ ሞሽን) በኤሌክትሮኒካዊ መንገድ ፋይል መደረግ ይኖርበታል፣ ወደ Civilefilings@dcsc.gov ኢመይል መደረግ ይኖርበታል።

- የፍትሐብሔር ክፍሉ፣ ለአካላቱ ተገቢ ማስታወቂያ በመስጠት፣ በጁሪ-ለማይዳኙ ክርክሮች (ናን-ጁሪ ትራያልስ) በርቀት ሊያከናውን ይችላል። ተጨማሪ ትእዛዝ እስከሚሰጥ ድረስ፣ የፍትሐብሔር ክፍል በጁሪ-የሚዳኙ ክርክሮች (ጁሪ-ትራያልስ) አያካሂድም። የፍትሐብሔር ክፍል በፍርድ ቤት በአካል የሚሰሙ በጁሪ-የሚዳኙ (ጁሪ-ትራያልስ) ወይም በጁሪ-የማይዳኙ ክርክሮች (ናን-ጁሪ ትራያልስ) ቀጠሮ በሚይዝበት ጊዜ፣ የክርክሩ ቀጠሮ የሚሰጠው ሁሉም አካላት በተገኙበት ችሎት ወይም ማንኛውም በፍርድ ቤት በአካል ከሚደረጉ በጁሪ-ከማይዳኙ ክርክሮች (ናን-

ጁሪ ትራያልስ) የቀጠሮ ቀን 30 ቀናት አስቀድሞ በጽሑፍ ማስታወቂያ በመስጠት፣ በጁሪ-የሚዳኝ ክርክር (ጁሪ-ትራያል) ከሆነ ደግሞ 60 ቀናት አስቀድሞ በጽሑፍ ማስታወቂያ በመስጠት ይሆናል፣ ይህ የሚሆነው ለጠበቆችና አካላት ምስክሮች በፍርድ ቤት መጥሪያ (ሰፒና) እንዲያመጡና ለክርክሩ እንዲዘጋጁ በቂ ጊዜ ለመስጠት ነው።

- የፍትሐብሔር ክፍል ማስረጃ የሚሰማባቸው ችሎቶች (ኤቪደንሻሪ ሂሪንግስ)፣ ዳኛ የሚዳኛቸው ክርክሮች (ቤንች ትራያልስ) ጨምሮ በማንኛውም አግባብ በሆነ ሁኔታ ችሎቶች በርቀት ያከናውናል።

- ሁሉም ከኪራይ ቤት የማስወጣቶችና (ኢቪክሽንስ) የመኖሪያ ቤት ሀራጅ (ፎርክሎዠር) የፍርድ ቤት ሂደቶች፣ እና የእዳ ስብሰባ (ዴት ኮሌክሽን) የፍርድ ቤት ሂደቶች ህግ እስከሚፈቅደው ድረስ ተግባራዊ ሳይሆኑ ይቆያሉ።

- ምክኒያቱም (1) ፍርድ ቤቱ የከመኖሪያ ቤት ማስወጣት ውሳኔዎች (ጃጅመንትስ ፎር ፖሰሽን ኤንድ ሪትስ ኦፍ ረስቲቱሽን) በፍትሀዊና ስርአቱ በጠበቀ መልኩ እየተፈጸሙ እንደሆነ የማረጋገጥ ተፈጥሮአዊ ስልጣን አለው፣ (2) ፍትሀዊና ስርአቱ የጠበቀ የከመኖሪያ ቤት ማስወጣት ትእዛዝ (ሪት ኦፍ ረስቲቱሽን) አፈጻጸም በማህበረሰብ ጤና አስቸኳይ ጊዜ ምክኒያት ለበርከት ያለ ጊዜ ከመኖሪያ ቤት ማስወጣቱ (ኢቪክሽን) የተላለፈ ሲሆን አከራዮች የከመኖሪያ ቤት ማስወጣቱ ቀጠሮ ሲሰጡ ምክኒያታዊ የሆነ ማስታወቂያ እንዲሰጡ ያስገድዳል፣ ነገር ግን በሙቀት ወይም በዝናብ ምክኒያት ለአጭር ጊዜ የተላለፈ ከሆነ ይህ ማድረግ አይጠበቅባቸውም፣ እና (3) በዲ.ሲ. ኮድ § 42-3505.01a በሚያዘው መሰረት የተለዋጩ ቀን ማስታወቂያ በመስጠት በኩል ምክኒያታዊ ያልሆነ ወይም ከባድ ጫና በአከራዮች ማሳረፍ የለበትም፣ በማርች 16፣ 2020 ወይም ከዚህ ቀን በኋላ ከመኖሪያ ቤት ለማስወጣት ቀጠሮ ተይዞለት የነበረ ህጉ እንዲቆይ የሚፈቅደው ጊዜ ካበቃ በኋላ ሌላ የከመኖሪያ ቤት ማስወጣት ቀጠሮ የተያዘለት ከሆነ ማንኛውም አከራይ የዲ.ሲ. ኮድ § 42-3505.01a በሚያዘው መሰረት የከመኖሪያ ቤት ማስወጣቱ ዳግም ቀጠሮ ከተያዘለት ቀን ቢያንስ ከ21 ቀናት በፊት ማስታወቂያ መላክ ይኖርበታል።

- የፍትሐብሔር ክፍል ተፈጻሚነታቸው ባልታገደ የኪራይ ቤት ማስወጣቶች (ኢቪክሽን)፣ መኖሪያ ቤት ሀራጅ (ፎርክሎዠር)፣ እና የእዳ ስብሰባ (ዴት ኮሌክሽን) ጉዳዮች የርቀት ችሎቶች ወይም በደረሱ ማመልከቻዎች ውሳኔ (ሩል ኦን ራይፕ ሞሽንስ) ሊያካሂድ ይችላል። እነዚህ ጉዳዮች በመይ 7፣ 2020 የእዳ ስብሰባ ጉዳዮች በተመለከተ የወጣው አጠቃላይ ትእዛዝ የማይመለከታቸው የአነስተኛ የይገባኛል ጉዳዮች (ስሞል ክለይምስ) ወይም የእዳ ስብሰባ ጉዳዮች እና የአከራይና ተከራይ ጉዳዮች ሕጋዊ ክልከላ (ስታቹቶሪ ሞራተርዩም) የማይመለከታቸው፣ እንዲሁም ደግሞ ሌሎች እንደነ መጥሪያ ማድረስ (ሰርቪስ ኦፍ ፕሮሰስ)፣ የአንድ አካል ብቻ በመስማት

መወሰን (ኤክስ ፓርተ ፕሩፍ)፣ እና የመከላከያ ትእዛዞች (ፕሮቴክቲቭ ኦርደርስ) የመሳሰሉ ተገቢ ሊሆኑ የሚችሉ የማመልከቻ ችሎቶች ወይም አጫጭር ማስረጃ የሚሰማባቸው ችሎቶች ያካትታሉ።

- ምንም እንኳን ፍርድ ቤቱ በመከላከያ ትእዛዝ (ፕሮቴክቲቭ ኦርደር) በሚያዘው መሰረት በአካል የሚደረጉ ክፍያዎች የመቀበል ውሱን ችሎታ ቢኖረውም፣ ተከራይ ***በጥሬ-ገንዘብ ያልሆነ*** ክፍያን ከሚከተሉት ዘዴዎች አንዱን በመጠቀም መክፈል ይችላል፡ (1) ክፍያዎን ወደ አከራይና ተከራይ ጸሀፊ ቢሮ (ክለርክ'ስ ኦፊስ) በፖስታ በመላክ፡ Landlord and Tenant Clerk's Office, 510 4th Street NW, Room 110, Washington, DC 20001፣ (2) ክፍያዎን በሞልትርየ ኮርትሀውስ በሚከተለው አድራሻ በሚገኘው ላቢ ባለው መጣያ ሳጥን (ድራፕ ባክስ) በማስገባት፡ 500 Indiana Avenue, NW, Washington, DC 20001፣ የመዝገብ ቁጥሩ (ኬዝ ናምበር) በክፍያው መጻፍ አለበት፣ (3) ክፍያዎን በኤሌክትሮኒካዊ መንገድ በፍርድ ቤቱ ፖርታል በኩል፣ ይህ የሚሆነው የወር ጠቅላላ ክፍያው ከ$1,000 የማይበልጥ ሲሆን ነው። እባክዎ ክፍያዎችን በኤሌክትሮኒካዊ መንገድ እንዴት መፈጸም እንደሚችሉ የወጣውን የጸሀፊ ቢሮዎች (ክለክር'ስ ኦፊስስ) አሰራር ማስታወቂያን ይመልከቱ፡ https://www.dccourts.gov/sites/default/files/Superior-Court-Clerks-Offices-Remote-Operations.pdf. ***በጥሬ ገንዘብ የሚደረጉ ክፍያዎች*** ፍርድ ቤቱ በውሱን ሁኔታዎች ሊቀበል ይችላል። ቀናትንና ሰአታትን በተመለከተ እባክዎ የጸሀፊ ቢሮዎች (ክለክር'ስ ኦፊስስ) ማስታወቂያን ይመልከቱ (ከላይ ያለውን ሊንክ ይጫኑ)። ተከራይ ክፍያውን በቀጥታ ለአከራይ ሊፈጽም ይችላል፣ አከራይ ከተከራይ በቀጥታ ክፍያ መቀበሉ እርምጃውን በፍርድ ቤት የመቀጠል ችሎታ አይገድበውም። ተከራይ የመከላከያ ትእዛዙን ማሻሻያ ካላገኘ እና ክፍያውን ወደ ፍርድ ቤት ሬጂስትሪ ወይም በአስቸኳይ ጊዜ በቀጥታ ለአከራይ ካልፈጸመ፣ እና አከራዩ በመቀጠል ማእቀቦች (ሳንክሽንስ) ይጣሉ ዘንድ ከጠየቀ፣ ፍርድ ቤቱ ከሌሎች ተያያዥነት ያላቸው ሁኔታዎች በተጨማሪ የህብረተሰብ ጤና አስቸኳይ ሁኔታ ጋር የተያያዙ አስቸጋሪ ሁኔታዎች ግምት ውስጥ ያስገባል።

- አስተዳደራዊ ትእዛዝ 06-17 (አድሚኒስትሬቲቭ ኦርደር 06-17) ምን ይበል ምን፣ የመጥሪያ ማድረሻ ቃለ ምስክርነቶች (አፊዳቪትስ ኦፍ ሰርቪስ) በአስቸኳይ ጊዜ ወቅት በኤሌክትሮኒካዊ መንገድ ፋይል ሊደረጉ ይችላሉ።

- አስተዳደራዊ ትእዛዝ 15-03 (አድሚኒስትሬቲቭ ኦርደር 15-03) ምን ይበል ምን፣ የመኖሪያ ቤት ሁኔታ ጥሰቶች ጉዳዮች እና እንደነ ወሳኝ ኩነት ሰነዶች የማሻሻል ማመልከቻዎች፣ የስም ለውጦች፣ የጾታ ምደባዎች (ጀንደር አሳይመንትስ)፣ የውጭ አገር የፍርድ ቤት መጥሪያ (ፎረይን ሰፒና)፣ የፍትሐብሔር የንብረት መውረስ (አሰት ፎርፈይቸር) አቤቱታዎች፣ የመረጃ ስም ማጥፋት (ሊበልስ ኦፍ ኢንፎርሜሽን)፣ እና ጓዳዊ ክሶች (ፍርየንድሊ ሱትስ) ጨምሮ ሁሉም በጃጅ ኢን ቻምበርስ የሚሰሙ

ጉዳዮች በአስቸኳይ ጊዜ ወቅት በኬዝ ፋይል ኤክስፐረስ በኩል በኤሌክትሮኒካዊ መንገድ ፋይል ሊደረጉ ይችላሉ።

- ደንብ 5 እና 5-III የሰፈረው ምን ይሁን ምን፣ ታትመው (ሲልድ) ያሉ ጉዳዮችና በመዝገብ ቁጥራቸው SLD የሚል ያለባቸው (ለምሳሌ፡2020 CABSLD 000001) በአስቸኳይ ጊዜ ወቅት ሰነዶች በኤሌክትሮኒካዊ መንገድ ፋይል መደረግ ይችላሉ። ባልታተመ (አንሲልድ) ጉዳይ የታተሙና (ሲልድ) ያልተቀነሰባቸው (አንሪዳክትድ) ሰነዶች ወደ ጸሀፊ ቢሮ (ክለርክ'ስ ኦፊስ) በወረቀት በፖስታ ወይም በመጣያ ሳጥን (ድራፕ ባክስ) በኩል መረከብ መቀጠል ይኖርባቸዋል።

- በርቀት የሚደረጉትን ችሎቶች ለማቀላጠፍ የፍትሐብሄር ክፍል ሁሉንም አካላት ሊገኙባቸው የሚችሉ እንደነ የቴሌፎን ቁጥሮችና ኢመይል አድራሻዎች የመሳሰሉ የመገኛ መረጃዎች ለፍትሐብሔር ክፍል ጸሀፊ ቢሮ (ክለርክ'ስ ኦፊስ) እንዲሰጡ ያበረታታል። እባክዎ የገዛ ራስዎትን ወይም የተቃራኒ አካልን የመገኛ መረጃ ለመስጠት ከታች ወዳሉት ኢመይል ያድርጉ ወይም ከታች ወደ ተዘረዘሩት ቁጥሮች ይደውሉ።

| | | |
|---|---|---|
| የፍትሐብሔር እርምጃዎች ቅርንጫፍ | CivilDocket@dcsc.gov | (202) 879-1133 |
| የአከራይና ተከራይ ቅርንጫፍ | LandlordandTenantDocket@dcsc.gov | (202) 879-4879 |
| የአነስተኛ የይገባኛል ጥያቄዎች ቅርንጫፍ | SmallClaimsDocket@dcsc.gov | (202) 879-1120 |

## የወንጀለኛ ክፍል (ክሪሚናል ዲቪዥን)

በፍርድ ቤቱ ካልታዘዘ በስተቀር በአስቸኳይ ጊዜ መፈጸም የነበረባቸው በህጎች፣ በፍርድ ቤት ደንቦች፣ እና ፍርድ ቤት ባስተላለፋቸውና በሌሎች ትእዛዞች የሰፈሩ የጊዜ ገደቦች የአስቸኳይ ጊዜ በስራ እስካለ ድረስ ተጨማሪ ትእዛዝ እስከሚሰጥ ድረስ ይታገዳሉ፣ ከተፈጻሚነት ለጊዜው ይቆማሉ (ቶል ይደረጋሉ)፣ እንዲሁም ደግሞ ይራዘማሉ። ይህ የሚከተሉትና ሌሎችን ያካትታል፡ በደንቦች (ሩልስ)5.1 እና D.C Code § 23- 1322(a) እና (b) መሰረት የተቀመጡ የመጀመሪያ ችሎቶች የጊዜ ሰሌዳዎች (ታይምላይንስ ፎር ፕረሊሚናሪ ሂሪንግስ)፣ እንዲሁም ደግሞ የሚከተሉትን ጨምሮ የክስ መመስረቻ የጊዜ ገደቦች (ኢንዳይትመንት ዴድላይንስ) እና የክርክር የጊዜ ገደቦች፣ እና በD.C. Code §§ 23-102, 23-1322(h), 24-801, and 24-531.01 et. seq. መሰረት የሰፈሩ የጊዜ ገደቦች።

ከዚህ ቀደም የተላለፉ የሚከተሉት ትእዛዞች ፍርድ ቤቱ ተጨማሪ ትእዛዝ እስከሚሰጥ ድረስ ተራዝመዋል፡

- በማርች 16፣ 2020 የተላለፈው የህግ አስከባሪዎች ለተጨማሪ ግለሰቦች በፍርድ ቤት መጥሪያ (ሳይቴሽን) እንዲፈቱ ፈቃድ የሚሰጥ ትእዛዝ።
- በማርች 21፣ 2020 የተላለፈው ህግ አስከባሪዎች ለተወሰኑ የቀላል ወንጀል የዳኛ እስር ትእዛዝ (ሚስደሚነር ቤንች ዋራንትስ) አይነቶች ቁጥጥር ስር ውስጥ ከማስገባት ይልቅ በፍርድ ቤት መጥሪያ (ሳይቴሽን) የመፍታት ስልጣን የሚሰጥ ትእዛዝ።
- በማርች 27፣ 2020 የተላለፈው የሳምንት መጨረሻ የእስር ፍርዶች (ዊከኤንድ ጀይል ሰንተንስስ) ያገደ ትእዛዝ።
- በኤፕሪል 1፣ 2020 የተላለፈው፣ ወደ ጎን ስለ ተተዉ ክሶች (ዲፈርድ ፕሮሰኩሺንስ) እና የፍርድ ስምምነቶች (ሰንተንሲንግ አግሪመንትስ) እና የፕሮቤሽን ዝርዝሮች (ፕሮቤሽናሪ ተርምስ) ጉዳዮች እየወደቁ ያሉ ጊዜያትን ሁኔታ በተመለከተ ለማብራራት የወጣው ትእዛዝ።
- የችሎቶች የጊዜ ሰሌዳ ስነ ስርአት ያቋቋመ የወንጀለኛ ክፍል ትእዛዝ (ስታንዲንግ ኦርደር)፣ በፍርድ ቤት 113 የችሎቶች የጊዜ ሰሌዳ ፕሮቶኮሎች ያቋቋመ ትእዛዝ (ስታንዲንግ ኦርደር) እና በኮቪድ-19 ወረርሽኝ ምክኒያት ከእስር ለመውጣት አስቸኳይ አቤቱታዎች ፋይል ማድረጊያ ስነ ስርአቶች ያቋቋመ ትእዛዝ (ስታንዲንግ ኦርደር)።

የወንጀለኛ ክፍል እንደሚከተለው ይሰራል፡

- የወንጀለኛ ክፍል በርቀት ወይም በከፊል በርቀት መስራቱን ይቀጥላል፣ ችሎቶች ከሰንትራል ሰልብሎክ፣ ዲ.ሲ. እስር ቤት (ጀይል)፣ ሰይንት ኤሊዛቤት ሆስፒታል፣ ዲፓርትመንት ኦፍ ዩዝ ሪሀብሊቴሽን ሰርቪስስ፣ ቢሮ ኦፍ ፕሪዝንስ እና ማህበረሰቡ በቴሌፎን ወይም ቪድዮኮንፈረንስ ይካሄዳሉ።

- በእስር-ያሉ የወንጀለኛ የመጀመሪያ ችሎቶች (ዲተይንድ ፕረሊሚናሪ ሂሪንግስ) እና ሌሎች ማስረጃ የማይሰማባቸው ችሎቶች (ናን-ኤቪደንሻሪ ሂሪንግስ) ተከላካይ ጠበቃ ከጠየቀና የዩናይትድ ስቴትስ ጠበቃ ጽህፈት ቤት ወይም የጠቅላይ አቃቤ ህግ ቢሮ ከተስማሙ መቀጠል ይችላሉ፣ ስምምነቱ ምክኒያታዊ ባልሆነ መንገድ መከልከል የለበትም።

- ሀያ የፍርድ ቤይ ክፍሎች በርቀት ወይም በከፊል በርቀት ስራቸውን ያካሂዳሉ፣ በዋናነትም የሚከተሉት ተግባራት በማከናወን ያተኩራሉ፡

  <u>በከፊል በርቀት የሚሰሩ የፍርድ ቤት ክፍሎች፡</u>

  - C-10 – የእምነት ክህደት ችሎቶች (አረይንመንትስ)፣ መቅረቦች

(ፕረዘንትመንትስ)፣ በፍርድ ቤት የእስር ማዘዣ ታስሮ መቅረብ (ቤንጅ ዋራንት ሪተርንስ)፣ ወንጀለኛን ወደ ሌላ ፍርድ ቤት ማስተላለፍ (ኤክስትራዲሽን)።

- 112 – በከፊል በርቀት የሚካሄዱ ተከላካዮች ማስረጃ-በማይሰማባቸው ችሎቶች ከዳኛው ጋር በፍርድ ቤት የሚቀርቡባቸው፣ ቅድመ-ክርክር (ፕሪ-ትራያል)፣ የፕሮቤሽን ምክንያት አሳይ (ፕሮቤሽን ሾው ከውዝ)፣ እና በዳኛ የእስር ፈቃድ መሰረት ወደ ፍርድ ቤት በአካል መምጣት (ዎክ ኢን ቤንች ዋራንትስ) ጨምሮ በእስር-የሌሉ የወንጀለኛ ጉዳዮች (ናን-ዲተይንድ ሂሪንግስ)።

- 203፣ 211፣ እና 215 – በከፊል ከርቀት የሚካሄዱ በእስር ያሉ ሲ.ኤፍ.1፣ ሲ.ኤፍ.2 እና ሲ.ኤፍ.3 ተከላካዮች ተቀባይነት ባለው ምርመራና የኮቪድ-19 ፕሮቶኮል ካለፉ በኋላ ከዳኛው ጋር በፍርድ ቤት የሚቀርቡባቸው የወንጀለኛ የመጀመሪያ ችሎቶች (ፕረሊሚናሪ ሂሪንግስ)።

- 201፣ 202 እና 316 – በከፊል ከርቀት የሚካሄዱ በእስር ያሉ በጁሪ-የማይዳኙ (ናን-ጁሪ) ችሎቶች እና የክስ ማጠናቀቂያ (ዲስፖሲቲቭ) የአቤቱታ ችሎቶች ተከላካዮች ተቀባይነት ባለው የኮቪድ-19 ፕሮቶኮል ካለፉ በኋላ ዳኛው ፊት በአካል ይቀርባሉ።

- ጠበቃ፣ የቅድመ-ክርክር አገልግሎቶች ተወካዮች፣ የፕሮቤሽን ኦፊሰሮች እና ሰለባዎች በአካል፣ ወይም ቪድዮ ወይም ቴሌፎን በመጠቀም በርቀት መቅረብ መቀጠል ይችላሉ።

- ምስክሮች በያንዳንዱ ጉዳይ በፍርድ ቤቱ እስከተፈቀደ ድረስ ቪድዮ ወይም ቴሌፎን በመጠቀም በርቀት መቅረብ ይችላሉ።

<u>በርቀት የሚሰሩ የፍርድ ቤት ክፍሎች፡</u>

- 111 – በርቀት የሚካሄዱ በእስር-የሌሉ የወንጀለኛ ጉዳዮች (ናን-ዲተይንድ ሂሪንግስ)፣ ወደ ጎን የተተዉ ክሶች (ዲፈርድ ፕሮሰኩሺንስ) ወይም የፍርድ ስምምነቶች (ሰንተንሲንግ አግሪመንትስ) በተመለከተ የተደረጉ ስምምነቶች ወይም የስምምነቶቹ ማጠናቀቅያ፣ የክስ ማጠናቀቂያዎች (ዲስፖዚሽንስ)፣ ምክኒያት አሳይ ችሎቶች (ሾው ከውዝ ሂሪንግስ) እና ፍርዶች (ሰንተንሲንግስ)።

- 115 – በርቀት የሚካሄዱ አስቸኳይ የቦንድ ምዘና ማመልከቻዎች ጨምሮ በእስር-ያሉ የወንጀለኛ መሰረታዊና ማስረጃ-የማይቀርብባቸው ጉዳዮች

(ሳብስታንቲቭ ናን-ኤቪደንሻሪ ማተርስ)።

- 210 – በርቀት የሚካሄዱ በእስር-ያሉ የወንጀለኛ ችሎቶች (ሪሞት ዲተንሽን ሂሪንግስ) እና ሌሎች በእስር ያሉ መሰረታዊ ማስረጃ-የማይሰማባቸው ጉዳዮች (ሳብስቴንቲቭናን-ኤቪደንሻሪ ማተርስ)።

- 213 – ጠዋት (ኤ.ኤም.) በርቀት የሚካሄዱ የክስ ማጠናቀቂያዎች (ዲስፖዚሽንስ)፣ የመጀመሪያ ችሎቶች መተዎች (ወይቨርስ ኦፍ ፕረሊሚናሪ ሂሪንግስ)፣ ፍርዶች (ሰንተንሲንግስ) ወዘተ ጨምሮ በእስር-ያሉ መሰረታዊና ማስረጃ-የማይቀርብባብቸው (ሳብስታንቲቭ ናን-ኤቪደንሻሪ) ጉዳዮች፣ ከሰአት ተከላካይ ሳይቀርብ የሚካሄዱ በእስር-ያሉ የመጀመሪያ የጊዜ ሰሌዳ ኮንፈረንስ (ኢኒሻል ስኬጁሊንግ ኮንፈረንስ)።

- 218 እና 311 – በርቀት የሚካሄዱ የመሰረታዊና ማስረጃ-የማይቀርብባብቸው ጉዳዮች (ሳብስታንቲቭ ናን-ኤቪደንሻሪ ማተርስ) በእስር ያሉ ከዲ.ዋይ.አር.ኤስ. እና ቢ.አ.ፒ. ጉዳዮች፣ እና ከጉዳዩ ዳኛ ፊት ያሉ በእስር-የሌሉ ጉዳዮች።

- 220 – በርቀት የሚካሄዱ አስቸኳይ-ያልሆኑ ፕሮቤሽን ምክንያት አሳይ ችሎቶች (ፕሮቤሽን ሾው ከውዝ ሂሪንግስ)።

- 312 እና 313 – በርቀት የሚካሄዱ፣ ወደ ጎን የተተዉ ክሶች (ዲፈርድ ፕሮሰኩሺንስ) ወይም የፍርድ ስምምነቶች (ሰንተንሲንግ አግሪመንትስ)፣ የክስ ማጠናቀቂያዎች (ዲስፖዚሽንስ) እና ፍርዶች (ሰንተንሲንግስ) በተመለከተ የተደረጉ ስምምነቶች ወይም የስምምነቶቹ ማጠናቀቅያ ጨምሮ ዩ.ኤስ.ኤ.አ. (312) እና አ.ኤ.ጂ. (313) ክርክር የሚደረግባቸው በእስር-የሌሉ የወንጀለኛ ችሎቶች (ናን-ዲተይንድ ሂሪንግስ)።

- 314 እና 321 –በርቀት የሚካሄዱ፣ በእስር-ያሉ የጊዜ ሰሌዳ ችሎቶች (ስኬጂሊንግ ሂሪንግስ)፣ ተከላካይ ላይገኝ ይችላል።

- 317 – በርቀት ከሰይንት ኤሊዛቤዝ ሆስፒታል የሚካሄዱ የአእምሮ ጤና ሁኔታ ትእዝብት የሚደረግባቸው (ሜንታል ኦብዘርቬሽን) እና ስምምነት ያልተደረሰባቸው የብቃት (ኮንተስትድ ኮምፐተንሲ) ችሎቶች።

በከፊል በርቀት በፍርድ ቤት ቁጥር 112 እና በርቀት በፍርድ ቤት ቁጥሮች 111፣ 115፣ 218፣ 220፣ እና 311 የተቀጠሩ የቅድመ-ክርክር እና ፕሮቤሽን ምክኒያት አሳይ (ሾው ከውዝ) ችሎቶች ወደ ሌላ ቀን አይሸጋገሩም። ሁሉም ሌሎች ፕሮቤሽን ምክኒያት አሳይ (ሾው ከውዝ) ችሎቶች ተለዋጭ ቀጠሮ ይሰጥባቸዋል፣ ኤ.ቪ.አር. ፋይል ቢደረግ የብሮቤሽኑ ማብቂያ ያቆማል (ቶል ይደረጋል)።

ሁሉም በእስር-ያሉና በእስር-የሌሉ (ዲተይንድ ኤንድ ናን-ዲተይንድ) ባሁኑ ጊዜ በርቀት ወይም በከፊል በርቀት የፍርድ ቤት ክፍሎች የችሎቶች ቀጠሮ ያላቸው ጉዳዮች ባሁኑ ጊዜ ተወስኖላቸው ባለ እለትና ሰአት ይቀጥላሉ።

ሁሉም በእስር-ያሉ ጉዳዩ ያለበት የሚታወቅባቸው ችሎቶች (ዲተይንድ ስታተስ ሂሪንግስ) በርቀት ወይም በከፊል በርቀት የፍርድ ቤት ክፍሎች ሳይሆን በሌላ የፍርድ ቤት ክፍሎች የተቀጠሩ ተለዋጭ ቀጠሮ መሰጠት የለባቸውም፣ በፍርድ ቤት 314 እና 321 በርቀት ሂደት ለማድረግ ቀጠሮው ወደ የጊዜ ሰለዴ ችሎት (ስኬጁል ሂሪንግ) ይቀየራል፣ በስድስተኛው የወንጀለኛ ክፍል የጊዜ ሰሌዳ ትእዛዝ (ክሪሚናል ዲቪዥን ስኬጁሊንግ ኦርደር) መሰረት ተከላካይ ላይቀርብ ይችላል።

በኦክቶበር 26፣ 2020 ወንጀለኛ ክፍል ከኖቨምበር 30፣ 2020 ጀምሮ በእስር-ያሉ በጁሪ-የማይዳኙ ክርክሮች (ዲተይንድ ናን-ጁሪ ትራያልስ) ለመቀጠል ፍላጎት እንዳለው የሚያሳይ የ30-ቀን ማስታወቂያ አቀረበ። ተከላካይ ጠበቃ ከጠየቀና የመንግስት ጠበቃ ከተስማማ፣ ምክኒያታዊ ባልሆነ መንገድም አልስማማም ማለት አይገባም፣ በጊዜ ሰሌዳ ችሎት (ስኬጁሊንግ ሂሪንግ) አዲስ የክርክር ቀናት ይመደባሉ።

ተጨማሪ ማስታወቂያ እስከሚሰጥ ድረስ የወንጀለኛ ክፍል በጁሪ-የሚዳኙ (ጁሪ-ትራያል) ክርክሮች አያካሂድም። የወንጀለኛ ክፍል በጁሪ-የሚዳኙ ክርክሮች ዳግም ከመጀመራቸው በፊት 60 ቀናት አስቀድሞ በጽሑፍ ማስታወቂያ ያሳውቃል፣ ይህ የሚሆነው አቃቤ ህግና ተከላካይ ምስክሮችን በፍርድ ቤት መጥሪያ (ሰፒና) እንዲያመጡና ለክርክሩ እንዲዘጋጁ በቂ ጊዜ ለመስጠት ነው። በ2020 የካላንደር አመት በጁሪ እንዲዳኙ ተቀጥረው ለነበሩ ሁሉም በእስር-ያሉ ጉዳዮች (ዲተይንድ ማተርስ) የክርክር ዝግጁነት ችሎቶች (ትራያል ሬዲነስ ሂሪንግስ) ቀጠሮ ይያዝላቸዋል፣ በዚሁ ቀጠሮ አዲስ የክርክር ቀን ሊመደብ ይችላል።

እስከ ጃንዋሪ 15፣ 2021 ተቀጥረው የነበሩ በጁሪ-የሚዳኙና በጁሪ-የማይዳኙ በእስር-የሌሉ ክርክሮች (ናን-ዲተይንድ ትራያልስ) በስድስተኛ የወንጀለኛ ክፍል የጊዜ ሰሌዳ ትእዛዝ መሰረት ወደሚቀጥለው ጉዳዩ ያለበት ደረጃ የሚሰማበት ተለዋጭ ቀጠሮ ይሰጠዋል።

ሁሉም ሌሎች እስከ ጃንዋሪ 15፣ 2021 ተቀጥረው የነበሩ የፍርድ ቤት መጥሪያ (ሳይቴሽን) እና የከባድ ወንጀል የእምነት ክህደት ችሎቶች (ፌለኒ አረይንመንትስ)፣ ፍርዶች (ሰንተንሲንግስ)፣ በእስር-የሌሉ ጉዳዩ ያለበት እና የቅድሚያ ችሎቶች (ናን-ዲተይንድ ስታተስ ኤንድ ፕረሊሚናሪ ሂሪንግስ) በስድስተኛ የወንጀለኛ ክፍል የጊዜ ሰሌዳ ትእዛዝ መሰረት የጉዳዩ ደረጃ ወደ ሚታይበት ቀን (ስታተስ ዴት) ይቀጥላሉ። ሁሉም አካላት በርቀት መቅረብ የሚችሉ ከሆነ፣ ችሎቱ ቀደም ባለ ጊዜ እንዲደረግ አካላቱ ከተስማሙ፣ አካላቱ ችሎቱ ቀደም ብሎ እንዲደረግ መጠየቅ ይችላሉ።

## የቤት ውስጥ ብጥብጥ ክፍል (ዶመስቲክ ቫዮለንስ ዲቪዥን)

በፍርድ ቤቱ ካልታዘዘ በስተቀር በአስቸኳይ ጊዜ መፈጸም የነበረባቸው በህጎች፣ በፍርድ ቤት ደንቦች፣ እና ፍርድ ቤት ባስተላለፋቸው እና በሌሎች ትእዛዞች የሰፈሩ የጊዜ ገደቦች የአስቸኳይ ጊዜ በስራ ላይ እስካለ ድረስ ተጨማሪ ትእዛዝ እስኪሰጥ ድረስ ይታገዳሉ፣ ከተፈጻሚነት ለጊዜው ይቆማሉ (ቶል ይደረጋሉ)፣ እንዲሁም ደግሞ ይራዘማሉ።

የቤት ውስጥ ብጥብጥ ክፍል (ዶመስቲክ ቫዮለንስ ዲቪዥን) እንደሚከተለው ይሰራል፡

- የቤት ውስጥ ብጥብጥ ክፍል (ዶመስቲክ ቫዮለንስ ዲቪዥን) የጸሀፊ ቢሮ (ክለርክ'ስ ኦፊስ) በርቀት ከ8:30 ኤ.ኤም. እስከ 5ፒ.ኤም. ድረስ ከሰኞች እስከ አርብ ይገኛሉ።

- ሁሉም ዳኞችና የፍርድ ቤት ክፍሎች ሰራተኞች በርቀት መስራት ይቀጥላሉ። በከፊል በርቀት በሚደረግ የፍርድ ቤት ክፍል በአካል እንዲቀርቡ ካልታዘዙ በስተቀር አካላት በዲ.ቪ.ዲ. የርቀት የፍርድ ቤት ክፍሎች በሚደረጉ ችሎቶች በቴሌፎን ወይም በቪድዮኮንፈረንስ መቅረብ ሊቀጥሉ ይችላሉ።

- በዲ.ቪ.ኤም. እና ሲ.ሲ.ሲ. ጉዳዮች ያሉ አካላት በኬዝ ፋይል ኤክስፐረስ በኩል በኤሌክትሮኒካዊ መንገድ ፋይል ማድረግ መቀጠል ይኖርባቸዋል። የፍትሐብሔር ፋይል የሚደረጉ ነገሮች በwww.probono.net/dccourts በኩል፣ ወይም ወደ DomesticViolenceManagement@dcsc.gov ኢሜይል በመላክ ሊደረጉ ይችላሉ።

<u>የወንጀለኛ ጉዳዮች</u> – የቤት ውስጥ ብጥብጥ ቀላል ወንጀል (ዶመስቲክ ቫዮለንስ ሚስደሚነር) (ዲ.ቪ.ኤም.) እና የፍርድ ቤት መድፈር ወንጀል (ክሪሚናል ኮንተምፕት) (ሲ.ሲ.ሲ.)

- የዲ.ቪ. ክፍል የወንጀለኛ የፍርድ ቤት ክፍሎች በርቀት ወይም በከፊል በርቀት መስራት ይቀጥላሉ። በርቀት የሚካሄዱ ችሎቶች ተከላካዮች ከዲ.ሲ. ጀይል ወይም ከማህበረሰቡ (ኮሚኒቲ) እየቀረቡ በቴሌፎን ወይም በቪድዮኮንፈረንስ ይካሄዳሉ። ጠበቃ፣ የቅድመ-ክርክር አገልግሎቶች ተወካዮች፣ እና የአሮቤሽን ኦፊሰሮች በአካል፣ ወይም ቪድዮ ወይም ቴሌፎን በመጠቀም በርቀት መቅረብ ይችላሉ። ምስክሮች በያንዳንዱ ጉዳይ በፍርድ ቤቱ እስከተፈቀደ ድረስ ቪድዮ ወይም ቴሌፎን በመጠቀም በርቀት መቅረብ ይችላሉ።

- <u>በእስር-ያሉ የጊዜ ሰሌዳ ችሎቶች (ዲተይንድ ስኬጁሊንግ ሂሪንግስ)</u>፡ በ C-10 በርቀት ፍርድ ቤት የተቀጠሩ በእስር-ያሉ ጉዳዩ ያለበት የሚታወቅባቸው ችሎቶች (ዲተይንድ ስታተስ ሂሪንግስ) ተለዋጭ ቀጠሮ አይሰጣቸውም። በነዚህ የጊዜ ሰሌዳ ኮንፈረንሶች (ስኬጁሊንግ ኮንፈረንስስ) ተከላካይ መቅረብ አያስፈልግም።

- <u>በእስር-ያሉ ማስረጃ-የሚሰማባቸው ችሎቶች (ዲተይንድ ሳንስታንቲቭ ሂሪንግስ)</u>፡ ተከላካይ በዲ.ቪ.ኤም. ወይም ሲ.ሲ.ሲ. ጉዳይ ምክኒያት በእስርቤት ያለ በእስር-ያሉ ችሎቶች (ዲተንሽን ሂሪንግስ) እና ሌሎች ማስረጃ-የማይሰማባቸው ችሎቶች በማክሰኞና ሀሙስ በርቀት በሚደረገው የዲ.ቪ.ዲ. የፍርድ ቤት ክፍል ይካሄዳሉ። ተከላካይ ከዲ.ሲ. እስር ቤት (ጀይል) ይቀርባል።

- በእስር-ያሉ በጁሪ-የማይዳኙ ክርክሮች (ዲተይንድ ናን-ጁሪ ትራያልስ)፡ በኖቨምበር 2፣ 2020 ዲ.ቪ.ዲ. ከዲሰምበር 2፣ 2020 ጀምሮ በእስር-ያሉ በጁሪ-የማይዳኙ ክርክሮች (ዲተይንድ ናን-ጁሪ ትራያልስ) መስማት ለመቀጠል የ30-ቀን ማስታወቂያ አቅርቦ ነበር። በእስር ያሉ ጉዳዮች በተመለከተ አካላቱ እንዴት መቀጠል እንደሚፈልጉ የሚሰማበት በርቀት የሚደረግ የጊዜ ሰሌዳ ችሎት (ስኬጁሊንግ ሂሪንግ) ለማዘጋጀት የፍርድ ቤት ጽህፈት ቤት (ቻምበርስ) አካላቱን ያገኛል። የተከላካይ ጠበቃ ከጠየቀና የመንግስት ጠበቃም ከተቀበለ፣ ምክኒያታዊ ባልሆነ መንገድ አልቀበልም ማለት የለበትም፣ አዲስ የክርክር ቀን ሊሰጥ ይችላል።

- የእምነት ክህደት ቃሎች (አረይንመንትስ)፡ የቤት ውስጥ ብጥብጥ የእምነት ክህደት ችሎቶች (አረይንመንትስ) በፍርድ ቤት ቁጥር C-10 መሰማት ይቀጥላሉ። የሲ.ሲ.ሲ. የእምነት ክህደት ችሎቶች (አረይንመንትስ) በአርብ ጠዋት በርቀት የዲ.ቪ.ዲ. የፍርድ ቤት ክፍል ይሰማሉ።

- <u>ምክኒያት አሳይ ችሎቶች (ሾው ከውዝ ሂሪንግስ)</u>፡

    - በከፊል በርቀት በሆነ ፍርድ ቤት የተቀጠሩ የቅድመ-ክርክርና የብሮቤሽን ምክኒያት አሳይ (ሾው ከውዝ) ችሎቶች አይራዘሙም። ተቀባይነት ያለው የኮቪድ-19 ፕሮቶኮል ካለፉ በኋላ ተከላካዮች ዳኛው ፊት በአካል ይቀርባሉ። ሁሉም ሌሎች አካላት በቴሌፎን ወይም በቪድዮኮንፈረንስ መቅረብ ይችላሉ።

    - ሙሉ በሙሉ በርቀት በሚሰራ የፍርድ ቤት ክፍል የተቀጠሩ የቅድመ-ክርክርና የብሮቤሽን ምክኒያት አሳይ (ሾው ከውዝ) ችሎቶች አይራዘሙም። ተከላካዮችም ጨምሮ ሁሉም አካላት በቴሌፎን ወይም በቪድዮኮንፈረንስ መቅረብ ይኖርባቸዋል።

    - ሁሉም ሌሎች ፕሮቤሽን ምክኒያት አሳይ (ሾው ከውዝ) ችሎቶች ተለዋጭ ቀጠሮ ይሰጣቸዋል። ኤ.ቪ.አር. ፋይል ቢደረግ የብሮቤሽኑ ማብቂያ ያቆማል (ቶል ይደረጋል)።

- ከእስር ለተለቀቁ ተከላካዮች የሚደረጉ ችሎቶች፡ በእስር-የሌሉ የወንጀለኛ ጉዳዮች (ናን-ዲተይንድ ማተርስ) በርቀት የሚደረጉ ችሎቶች አካላቱ ከጠየቁ በሰኞ፣ እሮብ፣ ወይም አርብ እለቶች በርቀት በሚካሄደው ፍርድ ቤት 118 ወይም 119 ሊካሄዱ ይችላሉ።

- <u>የተቀሩት ሁሉም ችሎቶች፡</u> ጉዳዩ ያለበት የሚታወቅባቸው ችሎቶች (ስታተስ ሂሪንግስ)፣ የአቅጣጫ መለወጥ (ዳይቨርዥን) ጉዳዮች፣ በእስር-የሌሉ የወንጀለኛ ክርክሮች (ናን-ዲተይንድ ትራያልስ)፣ እና ፍርዶች (ሰንተንሲንግስ) ጨምሮ እስከ ጃንዋሪ 15፣ 2021 ተቀጥረው የነበሩ ሁሉም ሌሎች የዲ.ቪ.ኤም. እና ሲ.ሲ.ሲ. ችሎቶች የሚዳኛቸው ዳኛ በሚያስተላልፈው የጊዜ ሰሌዳ ትእዛዝ (ስኬጁሊንግ ኦርደር) መሰረት ተለዋጭ ቀጠሮ ይሰጣቸዋል።

<u>የፍትሐብሔር መከላከያ ትእዛዞዝ (ሲቪል ፕሮቴክሽን ኦርደርስ)</u> (ሲ.ፒ.ኦ.ስ)

- በፍርድ ቤቱ የቤት ውስጥ ብጥብጥ ክፍል የሚካሄዱ የፍርድ ቤት ሂደቶች (ፕሮሰዲንግስ) ለህዝብ ክፍት ናቸው። አካላቱ ፍርድ ቤቱን በቀጥታ እንዴት መቀላቀል እንደሚችሉ መመሪያዎች ይሰጣቸዋል። አካላት-ያልሆኑ የዲ.ቪ. ክፍል ጸሀፊ ቢሮን (ክለርክ'ስ ኦፊስ) በ(202) 879-0157 በመደወል ወይም በ DVDhearings@dcsc.gov ኢሜይል በመላክ በፈለጉት ፍርድ ቤት እንዴት መቀላቀል እንደሚችሉ መረጃ ማግኘት ይችላሉ።

- በርቀት የሚካሄዱ ችሎቶች ለማቀላጠፍ ሁሉንም አካላት ሊገኙባቸው የሚችሉ እንደነ የቴሌፎን ቁጥሮችና ኢሜይል አድራሻዎች የመሳሰሉ የመገኛ መረጃዎች ለመስጠት ጸሀፊ ቢሮን (ክለርክ'ስ ኦፊስ) በቴሌፎን ቁጥር (202) 879-0157 ያገኙ ዘንድ የቤት ውስጥ ብጥብጥ ክፍል ያበረታታል። እባክዎ የገዛ ራስዎትን ወይም የተቃራኒ አካልን የመገኛ መረጃ ለመስጠት ይህንን የቴሌፎን ቁጥር ይደውሉ።

- የጊዝያዊ መከላከያ ትእዛዞች ጥያቄዎች በርቀት መሰማት ይቀጥላሉ።

- ዳኛው በምናብ በተደረገው ችሎት (ቨርቹዋል ሂሪንግ) ወይም በፍርድ ቤት ትእዛዝ በኩል ቲ.ፒ.ኦ.ውን ካላራዘበ በስተቀር፣ ሁሉም ጊዝያዊ የመከላከያ ትእዛዞች (ቲ.ፒ.ኦ.) የሚያበቁባቸው ቀናት ፕሪሳይዲንግ ዳኛ በኦገስት 14፣ 2020 ባወጣው የጊዜ ሰሌዳ ትእዛዝ መሰረት ይራዘማሉ።

- አካላቱ ቲ.ፒ.ኦ. እና ሌሎች ከጉዳዩ ተያያዥነት ያላቸው ወረቀቶች (እንደነ በሰው በኩል የፍርድ ቤት መጥሪያ ማድረሻ ሰነዶች) በኢሜይል ጭምር በኤሌክትሮኒካዊ መንገድ ይደርሳቸዋል።

- እንዲራዘም ማመልከቻ ካልቀረበ በስተቀር፣ ሁሉም በስራ ላይ ያሉ ሲ.ፒ.ኦ.ዎች ትእዛዙ ተግባራዊነቱ በሚያከትምበት ቀን ወይም በጁን 19፣ 2020፣ ከሁለቱም የኋለኛው ቀን፣ ተግባራዊነታቸው ያከትማል። በስራ ላይ ያሉ ተግባራዊነታቸው የሚያከትም የሲ.ፒ.ኦ. ጉዳዮች በማርች 19፣ 2020 እና መይ 14፣ 2020 ከተላለፉ የኮቪድ-19 ትእዛዞች ከነበረው የቤት ውስጥ ብጥብጥ ክፍል የተለዩ ናቸው፣ ነገር ግን በጁን 19፣ 2020 ከወጣ ትእዛዝ ተመሳሳይ መሆኑ ልብ ይበሉ።

- ክፍሉ ከኖቬምበር 9፣ 2020 ጀምሮ አስቀድሞ ተለዋጭ ቀጠሮ ተሰጥቷቸው የነበረ በፍትሐብሔር መከላከያ ትእዛዝ ካላንደር ያሉትን ሁሉንም ጉዳዮች መስማት ይጀምራል። ሁሉም የሲ.ፒ.ኦ. ክርክሮችና ተዛማጅ የሲ.ፒ.ኦ. ችሎቶች በኦገስት 14፣ 2020 በወጣው የሲ.ፒ.ኦ. የጊዜ ሰሌዳ ትእዛዝ (ስኬጁሊንግ ኦርደር) በሰፈረው ቀን ይካሄዳሉ። በተጨማሪ፣ አካላቱ ከጠየቁና ፍርድ ቤቱም ክፍት ቦታ ካለው፣ አካላት የሲ.ፒ.ኦ. ጉዳያቸው ከተመደው ቀን የቀረበ የችሎት ቀን መጠየቅ ይችላሉ።

<u>ከፍተኛ አደጋ መከላከያ ትእዛዞች (ኤክስትሪም ሪስክ ፕሮቴክት ኦርደርስ) (ኢ.አር.ፒ.ኦ.ስ)</u>

- የኤክስ ፓርተ (አንድ አካል ብቻ) እና የመጨረሻ ኢ.አር.ፒ.ኦ.ስ ጥያቄዎች መደረግ ይችላሉ፣ ሰነዶች ወደ DomesticViolenceManagement@dcsc.gov ኢመይል በማድረግ ሊደረጉ ይችላሉ። ማመልከቻው ከዲ.ሲ. የፍርድ ቤት ክፍሎች ድረገጽ ማግኘት ይቻላል። የተመደበው ዳኛ ጉዳዩን በርቀት ፍርድ ቤት ይሰማዋል።

- ፍርድ ቤቱ ካላዘዘ በስተቀር ሁሉም የኤክስ ፓርተ (አንድ አካል ብቻ) ኢ.አር.ፒ.ኦ. የሚያከትሙባቸው ቀናት ጉዳዩን እያየ ባለው ዳኛ በሚሰጠው የጊዜ ሰሌዳ ትእዛዝ መሰረት ይራዘማሉ።
- እንዲራዘም የሚጠይቅ ማመልከቻ ፋይል ካልተደረገ በስተቀር ሁሉም ተፈጻሚ እየሆኑ ያሉ ኢ.አር.ፒ.ኦ.ዎች በትእዛዙ በሰፈረው ማከተሚያ ጊዜ ተግባራዊነታቸው ያበቃል።

**<u>የቤተሰብ ፍርድ ቤት (ፋሚሊ ኮርት)</u>**

በፍርድ ቤቱ ካልታዘዘ በስተቀር፣ በአስቸኳይ ጊዜ መፈጸም የነበረባቸው በህጎች፣ በፍርድ ቤት ደንቦች፣ እና ፍርድ ቤት ባስተላለፋቸው እና በሌሎች ትእዛዞች የሰፈሩ የጊዜ ገደቦች የአስቸኳይ ጊዜ በስራ ላይ እስካለ ድረስ ተጨማሪ ትእዛዝ እስኪሰጥ ድረስ ይታገዳሉ፣ ከተፈጻሚነት ለጊዜው ይቆማሉ (ቶል ይደረጋሉ)፣ እንዲሁም ደግሞ ይራዘማሉ፣ <u>ይህ የማይሆነው፡</u>

<u>የበደል እና ቸልተኝነት ጉዳዮች፣ ተያያዥ ጉዳዮች</u>፡

በቸልተኝነት ጉዳዮች፣ የጉዲፈቻ ጉዳዮች፣ የወላጅነት መብቶች ማቆሚያ ጉዳዮች፣ እና የሞግዚትነት ጉዳዮች ማመልከቻዎች ልምድና ግኝት፣ በተመደበው ዳኛ ካልታዘዘ በስተቀር በሱፒርየር ፍርድ ቤት ተገቢ ደንቦች መመራቱ መቀጠል ይኖርበታል። ጉዲፈቻዎችና የሴፍ ፋሚሊ ህግ (ኤ.ኤስ.ኤፍ.ኤ.) የጊዜ ገደቦች ስራ ላይ መዋል ይቀጥላሉ።

የጉዲፈቻ አቤቱታዎች በኤሌክትሮኒካዊ መንገድ በመጣያ ሳጥን (ድሮፕ ባክስ) በ https://dcscgov.app.box.com/f/aeaf4eb2153743519a495d3f95d26c93 ፋይል መደረግ ይችላሉ። ሁሉም ሌሎች በጉዲፈቻ ጉዳዮች የሚደረጉ ልውውጦች በርቀት በኢ-ፋይሊንግ/ኬዝ ፋይል ኤክስፕረስ በኩል ፋይል ሊደረጉ ይችላሉ።

<u>የቤት ውስጥ ግንኙነት ጉዳዮች (ዶመስቲክ ሪሌሽንስ ኬዝስ)</u>፡

በተመደበው ዳኛ ካልታዘዙ በስተቀር፣ ጠበቆችና አካላት ማመልከቻዎችና ተቃውሞዎች ፋይል ማድረግን ጨምሮ የሚመለከታቸው የስርዓት ደንቦችን ማክበር ይጠበቅባቸዋል። ሁሉም በማርች 20፣ 2020 ወይም ከዚህ በኋላ በተሰጡ ትእዛዞች ያሉ የጊዜ ገደቦች ተፈጻሚ ይሆናሉ። ሁሉም ከማርች 20፣ 2020 በፊት በተሰጡ ትእዛዞች ያሉ የጊዜ ገደቦች በ90 ቀናት ተራዝመዋል።

ግለሰቦች ማህበራዊ ርቀትንና መጥሪያ ማድረስ (በአካልም ይሁን ሰርቲፋይድ ፖስታ ለማግኘት ወደ ፖስታ ቤት በመሄድ) "በቅንነት የሚደረግ ሙከራ" የማድረጋቸው እድል የመነመነ ስለሆነ፣ ፍርድ ቤቱ ተጨማሪ ትእዛዝ እስኪያስተላልፍ ድረስ፣ በደንብ 4(c)(3)(B) መሰረት በጽሁፍ መልእክት ወይም በኢመይል በመጠቀም በኤሌክትሮኒካዊ መንገድ ሰነዶችና መጥሪያ ማድረስ ይፈቀዳል። መጥሪያው የሚያደርስ አካል ለተመደበው ዳኛ በሚያረካ መንገድ ማድረሱን ማረጋገጥ ይኖርበታል፣ በኤሌክትሮኒካዊ መንገድ የተፈጸመው የማድረስ ዘዴ "ትክክለኛውን ማስታወቂያ ለመስጠት በምክንያታዊነት የተሰላ" መሆኑ የሚያሳይ መሆንን ያካትታል። በአካል ማድረስ በህግ፣ በዲ.ሲ. ኮድ §§ 13-332 (አቅመ አዳም ያልደረሱትን በአካል ማድረስ ያስገድዳል)፣ 13-333 (ብቁ ላልሆኑ ሰዎች በአካል ማድረስ ያስገድዳል)፣ እና 46-206 (ድጋፍ (ሳፖርት) የተመለከቱ ጉዳዮች በአካል ማድረስ ያስገድዳል) ጭምር፣ የተደነገገ ከሆነ አካላት በደንብ 4(c)(3)(B) መሰረት በኤሌክትሮኒካዊ መንገድ ማድረስ አይችሉም።

<u>የአእምሮ ተሀድሶ (ሜንታል ሀቢሊቴሽን) ጉዳዮች</u>፡

በአስተዳደር ትእዛዝ ቁጥር 00-06 መሰረት የምላሽ ሰጪዎች ጠበቆች የአሁናዊ ሁኔታ ሪፖርቶች ፋይል ማድረግ መቀጠል ይኖርባቸዋል፣ እስከሚቻል ድረስም የምላሽ ሰጪዎች መረጃ መሰረት ያደረገ በፈቃደኝነት የሚደረግ ቁርጠኝነት ፈቃድ ሪፖርት (ሪስፖንደንትስ ሪፖርትስ ኦን ኢንፎርምድ ኮንሰንት ፎር ቮሉንታሪ ኮሚትመንት) እና የተተኪ ውሳኔ ሰጪ ሪፖርቶች (ሳብስቲቱት ደሲሽን ሜከር ሪፖርትስ) ፋይል ማድረግ ይኖርባቸዋል። አካላት ልዩ ሪፖርት ወይም የተወሰነ ሰነድ ፋይል እንዲያደርጉ የሚያዝ ትእዛዝ ማክበር ይኖርባቸዋል። አካላት ማንኛውንም ነባር ትእዛዝ ማክበር ይኖርባቸዋል (a) ተሳታፊዎች ስብሰባ እንዲያደርጉ

የሚያዝ ወይም (b) ወረርሽኙ ግምት ውስጥ በማስገባት፣ በሚቻል መጠን ዲፓርትመንት ኦፍ ዲስኤቢሊቲ ሰርቪስስ የተወሰኑ አገልግሎቶች ወይም ድጋፍ እንዲያቀርብ የሚያዝ ትእዛዝ ማክበር ይኖርባቸዋል።

የቤተሰብ ፍርድ ቤት የሚከተሉት የችሎቶች አይነቶችን በርቀት በማካሄድ ይገኛል፡

<u>የበደል እና ቸልተኝነት ጉዳዮች፣ ተያያዥ ጉዳዮች</u>፡

- የቸልተኝነት የመጀመሪያ ችሎቶች (ነግለክት ኢኒሻል ሂሪንግስ)
- የአስቸኳይ ችሎቶች
- የክስ ማጠናቀቂያ (ዲስፖዚሽን) ችሎቶች
- የስምምነት ችሎቶች (ስቲፑሌሽን ሂሪንግስ)
- *ቲ.ኤ. ኤል. (Ta. L.)* ችሎቶች፣ ጉዲፈቻዎች፣ የወላጅነት መብቶች ማቆሚያ ማመልከቻዎች፣ እና የሞግዚትነት ክርክሮች ጨምሮ ማናቸውም አይነት ክርክሮች።
- የቤተሰብ እንክብካቤ ፍርድ ቤት ችሎቶች
- የቋሚነት ችሎቶች (ፐርማነንሲ ሂሪንግስ)፣ የክስ ማጠናቀቂያ ምዘና (ረቪው ኦፍ ዲስፖዚሽን) ችሎቶች፣ እና የቅድመ-ክርክር ችሎቶች ቀነ ቀጠሮ ይሰጣቸዋል
- ሌሎች ችሎቶች።

<u>የቤት ውስጥ ግንኙነቶች (ዶመስቲክ ሪሌሽንስ)</u>፡

- እንደየ የፍርድ ቤት ክፍል መገኘቱና ሌሎች ፍርድ ቤቱ ተገቢ ናቸው ብሎ የሚያስባቸው ነገሮች ግምት ውስጥ በማስገባት በስምምነትም ያለ-ስምምነትም የሚከናወኑ ፍቺዎች፣ መለያየቶች፣ ባለአደራነት፣ የልጅ ቀለብ።
- የቤት ውስጥ ግንኙነት በዛኑ ቀን የሚካሄዱ አስቸኳይ ችሎቶች (ሴም ደይ ኢመርጀንሲ ሂሪንግስ)።
- ባለአደራነት ለማሻሻል የሚደረጉ አስቸኳይ ማመልከቻዎች ወይም በዛኑ ቀን የሚደረግ አስቸኳይ ችሎት የተከለከለበት የፍርድ ቤት መድፈር ወንጀል (ኮንተምፕት)፣ ነገር ግን ማመልከቻውን ባፋጣኝ መስማቱ አስፈላጊና የሚቻል መሆኑ ፍርድ ቤቱ ድምዳሜ ላይ የደረሰ ከሆነ።
- እንደነ የግኝት አለመስማማቶች መፍታት ወይም ሌሎች ጉዳዮች፣ በርቀት መፈታት የሚችሉም፣ ወይም ለፍትህ ጥቅም አስፈላጊ ናቸው ተብለው የታመነባቸው፣ የመሳሰሉ በዳኛ አስተያየት የሚፈቱ ጉዳዮች (ዲስክረሺናሪ ማተርስ)።

<u>የወጣት ጥፋተኛ ሀላፊነት አለመወጣት (ጁቨናይል ደሊኲዌንሲ)፣ ክትትል የሚያስፈልጋቸው ሰዎች፣ እና የግል ጉዲፈቻዎች</u>፡

በፍርድ ቤቱ ካልታዘዘ በስተቀር በአስቸኳይ ጊዜ መፈጸም የነበረባቸው በህጎች፣ በፍርድ ቤት ደንቦች፣ እና ፍርድ ቤት ባስተላለፋቸው እና በሌሎች ትእዛዞች የሰፈሩ የጊዜ ገደቦች የአስቸኳይ ጊዜ በስራ ላይ እስካለ ድረስ ተጨማሪ ትእዛዝ እስከሚሰጥ ድረስ ይታገዳሉ፣ ከተፈጻሚነት ለጊዜው ይቆማሉ (ቶል ይደረጋሉ)፣ እንዲሁም ደግሞ ይራዘማሉ። ይህ ትዕዛዝ ቢኖርም፣ የቤተሰብ ፍርድ ቤት የሚከተሉት ችሎቶች ያከናውናል፡

- ሊመስል የሚችል ምክኒያት አሳይ ችሎቶች (ፕሮባብል ከውዝ ሂሪንግስ) ጨምሮ የወጣት ጥፋተኛ የመጀመሪያ ችሎቶች (ጁቨናይል ኢኒሻል ሂሪንግስ)።

- ዳኛው ችሎቱን ማካሄድ ጉዳዩን ለመፍታት ጠቃሚ ነው ወይም የጥፋተኛ ወጣቱ የእስር ጊዜ ሊቀይር ይችላል ብሎ በማመን ከወሰነ ማናቸውም ሌሎች ችሎቶች (ለምሳሌ፣ አስቸኳይ ችሎቶች፣ ጉዳዩ ያለበት የሚታወቅባቸው ችሎቶች (ስታተስ ሂሪንግስ)፣ የክስ ማጠናቀቂያ ችሎቶች (ዲስፖዚሽን ሂሪንግስ)) ሊደረጉ ይችላሉ፣ ይህ የሚመለከተው ለሆፕ (HOPE) እና ጁቨናይል ቢሀቭዮራል ዳይቨርሽን ፕሮግራም (ጀይ.ፒ.ዲ.ፒ.) የፍርድ ቤት ክፍሎች ነው።

- ለወጣት ጥፋተኞች እውነታ ለማወቅ የሚደረጉ ችሎቶች፣ በርቀት ብቻ እና ፍርድ ቤቱ በጉዳዩ እውነታ ለማወቅ የሚደረገውን ችሎት ለፍትህ ጥቅም ከፍተኛ ጉዳት ሳያደርስ ተጨማሪ ሊራዘም አይችልም የሚያስብል የተወሰኑ ምክኒያቶች ፍርድ ቤቱ የደረሰበት ከሆነ ብቻ፣ እና ከጠበቃ ጋር ከተመካከረ በኋላ በምላሽ ሰጪው ፈቃድ ብቻ የሚካሄዱ ናቸው። ማንኛውም አካል ምስክር ሊገኝ አይችልም ወይም በሱፐርየር ፍርድ ቤት የጥፋተኛ ወጣት ደንቦች (ጁቨናይል ሩልስ) መሰረት በማንኛውም ሌላ ምክኒያት እውነታ ለማወቅ የሚደረገውን ችሎት እንዲራዘም መጠየቅ ይችላል።

- ልዩ ስደተኛ ወንጀለኛ ወጣት (ስፔሻል ኢሚግራንት ጁቨናይል) ጉዳዩ ያለበት የሚታወቅባቸው ችሎቶች (ስታተስ ሂሪንግስ)።

- የግል ጉዲፈቻዎች።

<u>የአእምሮ ጤና</u>፡

- የአእምሮ ጤና ሊመስል የሚችል ምክኒያት ችሎቶች (ፕሮባብል ከውዝ ሂሪንግስ)።
- የአእምሮ ጤና ኮሚሽን ችሎቶች።

- የስረዛ ችሎቶች (ሪቮኬሽን ሂሪንግስ)፣ በሚያስፈልጉበት ጊዜ ጉዳዩ ያለበት የሚታወቅባቸው ችሎቶች (ስታተስ ሂሪንግስ)፣ አስቸኳይ ችሎቶች፣ ቅድመ-ክርክር ችሎቶች፣ እና ክርክሮች (ትራያልስ)።

<u>የአእምሮ ማገልመሻ (ሜንታል ሀቢሊቴሽን):</u>

- የአእምሮ ማገልመሻ ምዘና፣ እና አስቸኳይ ችሎቶች።

<u>የስም ለውጦች:</u>

- የስም ለውጥ ችሎቶች በመካሄድ ይገኛሉ።

<u>የወላጅነትና የድጋፍ (ፓረንቴጅ ኤንድ ሳፖርት) ጉዳዮች:</u>

- ሁሉም ቀነ ቀጠሮ እየተሰጣቸው ነው፣ የሚቻል ከሆነም በወረቀት ያሉትን በመፍታት ይገኛል።

<u>ጋብቻዎች:</u>

- የጋብቻ ስነ-ስርአቶች መፈጸም ዳግም ተጀምሯል፣ እና በዌብኤክስ በኩል እየተፈጸሙ ነው። የጋብቻ ምስክር ወረቀት የምትፈልጉ አካላት እባካችሁ የሚከተለውን ጎብኙ: https://www.dccourts.gov/form/marriage-application

<u>ሌላ ተዛማጅነት ያለው መረጃ:</u>

- በቤተሰብ ፍርድ ቤት አዲስ የቤት ውስጥ ግንኙነቶች አቤቱታዎች ወይም ማመልከቻዎች ፋይል የማድረግ ሂደት በዝርዝር በፍርድ ቤቱ ድረገጽ ይገኛል፣ በ https://www.dccourts.gov/sites/default/files/DRB-Case-InitiationInstructions-for-filers.pdf ይመልከቱት።

- የቤተሰብ ፍርድ ቤት ራስ-አግዝ ማእከል (ፋሚሊ ኮርት ሰልፍ-ሄልፕ ሰንተር) (202-879-0096) በቤተሰብ ፍርድ ቤት ጉዳዮች (ፍቺ፣ የልጅ ባለአደራነት (ቻይልድ ካስተዲ)፣ የልጅ ቀለብ፣ ወዘተ) መረጃ ለመስጠትና አካላት ሰነዶች ፋይል ማድረግ እንዲችሉ ለመርዳት በርቀት ይሰራል።

- ፍርድ ቤቱ የፍርድ ቤት መጥሪያዎች በኢሌክትሮኒካዊ መንገድ ይሰጣል፣ ፋይል ወዳደረገ አካልም በኢመይል ይልካል።

- የቤት ውስጥ ግንኙነቶች የመጀመሪያ ችሎት ቀን (ኢኒሻል ሂሪንግ) ፋይል በሚደረግበት ጊዜ ቀነ ቀጠሮ አይሰጥም፣ ምላሽ ሰጪ ሰነድ ፋይል ካደረገ ወይም ሰነዶች እንደደረሱ የቃለ መህላ ማረጋገጫ (አፊዳቪት ኦፍ ሰርቪስ) ፋይል ከተደረገ በኋላ፣ እና የፍርድ ቤቱ አሰራሮች ደረጃ ግምት ውስጥ በማስገባት ሊደረግ የሚቻል ከሆነ ነው ቀጠሮ የሚሰጠው።

- ክትትል የሚደረግበት የጉብኝት ማእከል (ሱፐርቫይዝድ ቪዚቴሽን ሰንተር) የመግቢያ ቃለ ምልልሶችና (ኢንቴክ ኢንተርቪውስ) ክትትል የሚደረግባቸው ጉብኝቶች በርቀት በማካሄድ ላይ ይገኛል።

- ባለ ብዙ-በር (መልቲ-ዶር) ሽምግልና እና የሽምግልና ምዝገባ በቪድዮኮንፈረንስ ወይም በቴሌፎን መሳተፍ ለሚችሉ አካላት በርቀት መደረግ ይችላል።

<u>**የግብር (ታክስ)፣ እና የኑዛዜ ወይም ውርስ ህጋዊነት ማረጋገጫ (ፕሮቤት) ክፍሎች**</u>

በኦገስት 13፣ 2020 የዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ዋና ዳኛ (ቺፍ ጃጅ) በዲ.ሲ. ኮድ እና በሱፒርየር ፍርድ ቤት ደንቦች ያሉ ሁሉም የህግና ደንብ-ተኮር የጊዜ ገደቦች እስከ ኖቨምበር 9፣ 2020 እንዲታገዱ፣ ለጊዜው ከተፈጻሚነት እንዲቆሙ (ቶል እንዲደረጉ) እና ተራዝመው የሚቆዩበት የጊዜ ገደብ ለማራዘም የሚያስችል የተሻሻለ ትእዛዝ አስተላልፏል።

በግብር (ታክስ)፣ እና በኑዛዜ ወይም ውርስ ህጋዊነት ማረጋገጫ (ፕሮቤት) ክፍሎች የነበረ እግድ አሁን ተነስቷል፣ እና በዲ.ሲ. ኮድ እና በሱፒርየር ፍርድ ቤት ደንቦች ያሉ ሁሉም የህግና ደንብ-ተኮር የጊዜ ገደቦች ባሁኑ ሰአት በሙሉ ሀይል ተግባር ላይ ይውላሉ። ፋይል የሚያደርጉ አካላት ይህን ትእዛዝ ከተላለፈበት ሰአት ጀምሮ ባሉ ስልሳ (60) ቀናት ውስጥ ማናቸውም በተሻሻለው የዋና ዳኛ (ቺፍ ጃጅ) ትእዛዝ መሰረት ከተፈጻሚነት ቆመው የነበሩ (ቶል ተደርገው የነበሩ) ማናቸውም ፋይል መደረግ ያለባቸው ነገሮች ፋይል ማድረግ ይችላሉ ወይም ተጨማሪ ጊዜ እንዲሰጣቸው በጉዳዩ ለተመደበው ዳኛ መጠየቅ ይችላሉ።

የኑዛዜ ወይም ውርስ ህጋዊነት ማረጋገጫ ክፍል (ፕሮቤት ዲቪዥን) እንደሚከተለው ይሰራል፡

- ዳኞች የሚከተሉትን ጉዳዮች በርቀት በዌብኤክስ ይሰማሉ፡
    - የ21-ቀን አስቸኳይ ሞግዚቶች (ኢመርጀንሲ ጋርድያንስ)— በኢመይል (ጠበቆችና ራሳቸውን-የወከሉ ፋይል አድራጊዎች) እና በቴሌፎን (ራሳቸውን-የወከሉ ፋይል አድራጊዎች ብቻ) ፋይል የተደረጉ

- ○ የ90-ቀን የጤና-ጥበቃ ሞግዚቶች (ሄልዝ-ኬር ጋርድያንስ)— በኢመይል (ጠበቆችና ራሳቸውን-የወከሉ ፋይል አድራጊዎች) እና በቴሌፎን (ራሳቸውን-የወከሉ ፋይል አድራጊዎች ብቻ) ፋይል የተደረጉ

- ○ የአጠቃላይ የፍርድ ቤት ሂደት ማመልከቻዎች (ፐቲሽንስ ፎር ጀነራል ፕሮሲዲንግስ) (የሞግዚትነት እና ተንከባካቢነት ማመልከቻዎች (ጋርድያን ኤንድ ኮንዘርቫቶርሺፕ ፐቲሽንስ)) – በኢመይል (ጠበቆችና ራሳቸውን-የወከሉ ፋይል አድራጊዎች) እና በፖስታ (ጠበቆችና ራሳቸውን-የወከሉ ፋይል አድራጊዎች) ፋይል የተደረጉ

- ○ ዳኛው በዌብኤክስ በመጠቀም በርቀት ሊሰሙ ይችላሉ ብሎ የወሰነባቸው ሌሎች የጣልቃገብነት ጉዳዮች (ኢንተርቬንሽን ማተርስ)

- ○ ዳኛው በዌብኤክስ በመጠቀም በርቀት ሊሰሙ ይችላሉ ብሎ የወሰነባቸው የንብረት ጉዳዮች (ኢስቴት ኬዝስ) ጨምሮ፣ ሌሎች የኑዛዜ ወይም ውርስ ህጋዊነት ማረጋገጫ ጉዳዮች

- የሞግዚትነት ቀጠሮዎች ሶስት ዓመታዊ ግምገማዎች ታግደዋል።

የግብር ክፍል (ታክስ ዲቪዥን) እንደሚከተለው ይሰራል፡

- ምክኒያት አሳይ (ሾው ከውዝ) እና ጉዳዩ ያለበት ሁኔታ (ስታተስ ሂሪንግ) ችሎቶች በዌብኤክስ በኩል በርቀት ይካሄዳሉ

- የመጀመሪያ የጊዜ ሰሌዳ (ኢኒሻል ስኬጁሊንግ)፣ የቅድመ-ክርክር (ፕሪ-ትራያል) ኮንፈረንሶች፣ እና ክርክሮች (ትራያልስ) በዌብኤክስ በኩል በርቀት ይካሄዳሉ

## <u>የኦዲተር ማስተር ቢሮ</u>

ኦዲተር ማስተር ሁሉንም ችሎቶች በርቀት በዌብኤክስ በኩል እያካሄደ ነው። አካላት በቴሌፎን ወይም በቪድዮ-ኮንፈረንስ መሳተፍ ይችላሉ። በርቀት እንዴት መሳተፍ እንዳለብዎ የሚያሳዩ መመሪያዎች ለሁሉም አካላት ይሰጣሉ።

ኦዲተር ማስተር ከኦገስት 1፣ 2020 ጀምሮ ያስተላለፋቸውን ሁሉም ትእዛዞች አካላት ማክበር ይኖርባቸዋል። ቢሮው ባሁኑ ሰአት አስቀድመው ተቀጥረው የነበሩ የሁሉንም ችሎቶች ሌላ ቀን ቀጠሮ የሚሰጥ ትእዛዝ፣ በአዳዲስ ጉዳዮች የችሎቶች ቀን ቀጠሮ፣ እና ሰነዶች የሚቀርቡባቸው አዳዲስ ቀናት የያዙ የተለዩ ትእዛዞችን በመስጠት ይገኛል።

ሰራተኞች በርቀት ከ8:30 ኤ.ኤም. እስከ 5:00 ፒ.ኤም. ከሰኞ እስከ አርብ ይገኛሉ። ሰራተኞች ሁሉንም ሰነዶች በርቀት ሂደት እያደረጉ እንደሆነ ልብ ይበሉ። ሰነዶች በኢሜይል ለAuditor.Master@dcsc.gov ወይም በፖስታ ለ፡ Office of the Auditor-Master, 500 Indiana Avenue NW, Washington, DC 20001 ማስረከብ ይችላሉ። በሚስጢር መያዝ የሚኖርባቸው (ሰንሲቲቭ ኢን ኔቸር) ሰነዶች በኢሜይል በኩል ወደ AMFinancialBox@dcsc.gov መላክ ይቻላል።

ሁሉም ችሎቶች የተደረጉባቸውና ሁሉም ሰነዶች የተረከቡባቸው ጉዳዮች በተመለከተ ሪፖርቶች በመዘጋጀት ይገኛሉ። ሪፖርቶች እንደተጠናቀቁ ለአካላት እንዲደርሱ ይደረጋሉ።

ጥያቄዎች ቢኖርብዎ እባክዎ ቢሮውን በቴሌፎን ቁጥር 202-626-3280 ወይም በኢሜይል በAuditor.Master@dcsc.gov ያግኙ።